# ለሆዳቸው ያደሩ፣ የከሃዲዎችንና የወያኔ መሳሪያ የሆኑትን ባሕርያቸውንና ማንነታቸውን አውቀን በጽናት እንታገል

ከኃይለ ልዑል ግርማ
ዋሽንግተን ዲሲ

የወያኔ ዘረኛና አምባገነነን አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት፣ በጎሳና በቋንቋ ሕዝቡን በመከፋፈል፣ የሥልጣን እድሜውን ለማራዘም የተጠቀመባቸውን የተንኮል መንገዶች በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቃውሞና እምቢተኛነት የከሸፈ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ለሆዳቸው ባደሩ፣ ለጥቅም በተገዙ፣ ተቃዋሚውን ከድተው ለወያኔ ባደሩ ግለሰቦች አማካኝነት የተንኮል መርዙን በመሃላችን እያስረጨብን ይገኛል።

ወያኔ ለስለላና አፈና፣ ለድለላና ማወናበጃ የሚሆን ከፍተኛ የሆነ የአገሪተን ገንዘብ ያጠፋል። በ1998 ዓ.ም ያወጣው ባለ 52 ገጽ መመሪያ ዋናው ዓላማም ይኸው ነው። የሕዝብ ሀብትን ሕዝብን ለማፈን ሲጠቀምበት አንዳንድ መንፈሰ ደካማ የሆኑ ሰዎች ለጥቂት ጊዜ መጠቀሚያ በመሆን ሆዳቸውን ከሞሉ በኋላ አንቅሮ ለሚተፋቸው ሲስገበገቡ፣ ሕሊናቸውን፣ ታሪካቸውንና ስማቸውን ሲበክሉ ሲያጠፉ ይታያሉ። ዞሮ ዞሮ ራሳቸውን በጊዜያዊነት የጠቀሙ ቢመስላቸውም ወያኔን በመደገፋቸው የወገናቸውን ስቃይና መከራ እድሜ እያራዘሙ መሆኑን፣ አገራቸውን እየገደሉ መሆናቸውን መገንዘብ አለባቸው። ወደፊት ከወያኔ እኩል ተጠያቂም ይሆናሉ። ስማቸውንና ድርጊታቸውን መከታተልና ለነገ ተጠያቂነት በዶክመንት መያዝ የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

ከምርጫ 97 በኋላ ወያኔ 131 ሰዎችን ማለትም የቅንጅት መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችንና የሰብዓዊ መብት ተሚጋቾችን በዘር ማጥፋትና በሀገር ክህደት ወንጀል ሲከሳቸው አጠቃላይ የሀሰት ክሱ ሁኔታ የሚያስቅ ድራማ መሆኑ ቢታወቅም፣ በድራማ ውስጥ ደግሞ ሌላ ድራማም እየተሰራ ነበር። ከእውነተኛ መሪዎቹና በሀሰት ተከሳሾች ጋር በመደባለቅ የወያኔን ተላላኪዎችና ሰርጎ ገቦችንም "በዘር ማጥፋት ወንጀልና በአገር ክህደት" ከሷቸው ነበር። ያ ሆን ተብሎ የተደረገው የእነዚያን ሰዎች ስም በተቃዋሚ ክፍሎች ዘንድ የሀሰት ዝና በመፍጠር፣ ውስጥ ለውስጥ የሚሰሩት ሴራና ደባ እንዳይጋለጥ መሸፈኛ የሀሰት ክስ ነበር። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ እነ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ብርሃነ መዋ፣ ዳዊት ከበደ፣ ኤልያስ ክፍሌ፣ ዳንኤል አሰፋ፣ ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም፣ ክፍሉ ታደሰ፣ ታማኝ በየነ ሰለሞን ተካልኝ ወዘተ ..ሲሆኑ ዛሬ እነዚህ ሰዎች አቂማቸው ከወያኔ ጎራ እንደሆኑ ስራቸው እየመሰከረባቸውና እንደሆነ ሕዝብ እያየው ነው። የእነርሱ የበላይ የሆነው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው።

የእነዚህ ሰዎች መከሰስ በውጭ የሚያደርጉትን ደባና ተንኮል ሽፋን ሰጥቶት፣ ጸረ ወያኔ ትግል ላይ ቀዝቀዛ ውሃ ሲያፈሱና ሲያዳፍኑ አስቀድሞ ወያኔ ከስሻቸዋለሁ በማለቱ ተቃዋሚው ጎራ አምኗቸው ስለነበር ተታለለ። ግራም ተጋባ። ለአበዛኞቻችን ሴራውና ደባው የገባን ዘግይቶ ነው። ደግነቱ ዛሬ የአንድነት ኃይሉ ይህንን በሚገባ አውቆ በውስጥም በውጭም በቆራጥነት በመፋለም ላይ ይገኛል።

የመጀመሪያ ሥራቸውን ሲጨርሱ ማለትም በአሉባልትና በሰርጎ ገብነት ትግሉን ካዳከሙና ክፍፍል ከፈጠሩ በኋላ፤ ዛሬ ደግሞ ስልቱን ቀይረው "ከወያኔ ጋር አብሮ መስራት ይቻላል"፣ "መቻቻል" ይቻላል በማለት ለወያኔ ግድያና ተጠያቂነት ከለላ የሚፈጥሩ፣ "በምርጫ 2010 ገብተን ማሸነፍ እንችላለን" እያሉ የሚደልሉ፣ የወያኔን የኢኮኖሚ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻን በዜና ማሰራጫዎች እያስተላለፉ የአገር ቤቱ ኤኮኖሚ በዚህን ያህል ፐርሰንት አድጓል በማለት የሚያራግቡና የተሳሳተ መረጃ የሚሰጡ፣ ለተወሰነ ካሬ ሜትር ቦታ እንዲመሩ በውጭ ያለውን ነዋሪ የሚገፋፉና በዚያች 500 ኬሬ ሜትር በማትሞላ ጥቅም ተይዞ ለሕዝብ ትግል መቆምና መታገሉን ለማፈን የሚደልሉ፣ የሥራና የንግድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በወያኔ ኤኮኖሚ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆንና የእነርሱን ንግድ ሽፋን ሆኖ ወያኔን ለመጥቀም የሚደረግ ስውር ደባን የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ ከባሕልና ከአስተሳሰባችን ውጭ የሆኑ ርካሽ የውጭ ባህሎችን በስልጣኔ ስም በወጣቱ ዘንድ በቪዲዮ፣ በጭፈራ ዝግጅትና በመሳሰሉት እንዲለመዱ ማድረግ፣ በተቃዋሚው ጎራ ደግሞ ተለጣፊ ድርጅትን መፍጠር፣ መከፋፈሉን ማጠናከርና አገር ወዳዱ ሞራሉ እንዲነካና እቤቱ አርፎ እንዲቀመጥ ተስፋ አስቆራጭ አሉባልታ መንዛት፣ ጠንክሮ

የሚታገለውን ደግሞ የተለያዩ አማላጆችን በጋደኛ፣ በዘመድ "በሃይማኖት አባቶች" በማስጠየቅ አርፎ እንዲቀመጥ በማድረግ ትግሉን ማዳፈን ነው የያዙት።

እነዚህ በተቃዋሚ ስም ተለጣፊ በመፍጠር ወያኔን የሚያገለግሉ፣ አገር ቤት ኢንቨስትመንት ያላቸው፣ ለመግባት ያሰፈሰፉና የተሰረቀው የሕዝብ ድምፅ እንደተሰረቀ ሆኖ ለምርጫ 2010 እንዘጋጅ የሚሉ ከሃዲዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ የሚሰሩ የውስጥ ጠላቶች ናቸው። እናስታውስ፤ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በኤርፖርት ተሸኝቶ የወጣ ወያኔ፣ ብርሃነ መዋ በኬንያ አድርጎ በ2 ሳምንቱ አሜሪካ የገባ እና ንብረቱና ንግዱ አሁንም አገር ቤት የሚካሄድለት የወያኔ መልዕክተኛ፣ ዳንኤል አሰፋ ያልተያዙት የቅንጅት መሪዎች ታድነው ሲያዙ እርሱ በኤርፖርት ተሸኝቶ ሲንጋፖር ከዚያ አሜሪካ መጥቶ የቀረ ግለሰብ፣ ክፍሉ ታደሰ ከምርጫው በኋላ ወያኔ ሸኝቶት በኤርፖርት ወጥቶ አሜሪካ የገባ "ለውጭ መንግሥት የሚሰራ" ነው። የእነዚህ ሁሉ ሰዎች አወጣጥ ተመሳሳይ ነው። ወያኔ በአገር ቤቱ ያለውን እኛ እንመታዋለን እናንተ የውጭውን ትግል አፈራርሱ ተብለው የተላኩ ናቸው።

አቶ ታማኝ በየነ ደግሞ "መቻቻል"፣ "እርቅ"፣ "2010 ምርጫ" ወዘተ... እያለ የሚቀባጥር፣ ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ባለ በእነ አላሙዲንና ሌሎች የወያኔ ተላላኪዎች ቴሌቭዥን ጣቢያ የእነ ብርሃነ መዋ የፕሮፓጋንዳ ማሽን ሆኖ ሲሰራ የከረመ፣ ተቃዋሚውን የሚከፋፍል የተቃዋሚ መሪዎችንና ሀቀኛ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በሀሰት የሚወነጅል፣ የሚዘልፍና የሚያዋርድ ግለሰብ ነው። ሥራው እጅግ ያሳፍራል። ለቅንጅት ትግል ተሳትፎ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ለመገኘት በሺህ ዶላሮች የሚያስከፍል (እንደ አገራችን አስለቃሽ ገንዘብ ተከፍሎት)፣ ለቅንጅት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት እጅግ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍልና የራሱን ጥቅም ብቻ የሚያሳድድ ነው። እሱን ብሎ የቅንጅት ደጋፊ። ታማኝ እኮ የአላሙዲን አጫዋች ነው። በቅርቡ ደግሞ ፕሮፌሰር ይስሐቅ የጀመረውን ስራ በመቀጠል የወዶ ገቦች ምልመላ ሲያደርግ ሶስት ቀን ሙሉ ሲዶልቱ የነበረውን ሴራ ታማኝ በየነ "እንደው ሻይ ቡና ለማለት ከፕሮፌሰር ይስሐቅ ጋር ተገናኝተናል" ሲል ነገሩ አቃሎ ለመናገር ቢሞክርም ውሸቱ በጥያቄ ተጋልጦ እውነቱ እዚያው ወጥቶ መናገር አቅቶት እምባ እምባ ሲለውና አፉ ሲተሳሰር ተሰምቷል። ታማኝ ከምርጫ 97 በኋላ በተቃዋሚው ክፍል ዘንድ ለጥቂት ጊዜ ሆይ ሆይ ብሎ ወያኔም ዝነኛ ሊያደርገው "የሀገር ክህደትና የዘር ማጥፋት ወንጀለኛ" ስሙን ስለጠቀሰለት ጉራው ለጉድ ነበር። እጆቹን ኪሶች ውስጥ ከትቶ ወያኔ "በዘር ማጥፋት እኔን ከሶኛል" እያለ ሆዳችንን ሲበላን ነበር። አዬ ታማኝ፣ ታማኝ አልነበረም። ለገንዘብ ሕዝቡንና ትግሉን ሸጧል። የውስጥ ሥራውን መሥራት ከጀመረ ለካስ ቆይቷል።

ከእነዚህ የሀሰት ተቃዋሚዎች ወይም የወያኔ የውስጥ መልዕክተኞች መሀከል ሻዕቢያው ኤልያስ ክፍሌም "በዘር ማጥፋትና በሀገር ክህደት" ተከሶ ነበር። እንዲያውም ሼክ አላሙዲንም ከሶኛል እያለም ማስወራት ጀምሮ ነበር። ኤልያስ ክፍሌ መቼም እራሱን የማያደርገው፣ የማይገባበት ነገርና ቦታ የለም። ለመሆኑ ኤልያስ ክፍሌ ሙያው ምንድነው ሥራውስ ምንድነው ተብሎ ቢጠየቅ የወያኔና የሻዕቢያ አገልጋይነት በቀር ሌላ እንደሌለው የታወቀ ነው። ሆኖም ግን በእርሱ ላይ ወያኔ ያቀረበው ክስ መሸፈኛ የሆነ ድራማ ነው።

ሌላው ሰለሞን ተካልኝ የተባለው አሳፋሪ ግለሰብ በዚሁ በዘር ማጥፋትና በሀገር ክህደት ተከሶ ነበር። ክሱ ሳይነሳለትና ምንም ሳይነገር አዲስ አበባ ሼራተን ሆቴል መታየቱ ተነገረ። የደረሰበትን ሰምተናል። ሕዝብ ግን እንደጠላው፣ ምራቁን እንደተፋበት፣ እንደሰደበው ይኖራል። የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ወያኔ "ያሰረው"፣ "የከሰሰው"፣ "የሚፈለግ"፣ "ያንገላታው"፣ "የደበደበው"፣ እየተባለ በማስነገር ቅጥረኞቹን በመካከላችን እንዳሰማራቸው ለማሳወቅ ነው። በስደተኞችም ስም እየላካቸው አብረውን እየተጋፉ ተልዕኮውን የሚፈጽሙ መኖራቸውን በሚገባ መገንዘብ አለብን። በዚህ ጉዳይ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ።

አሁንም በኃይማኖት ተቋማትና በኮሚኒቲ ውስጥም ሰርገው በመግባት ወያኔያዊ ተልዕኮቸውን የሚፈጽሙ በየከተማው አሉ። ስማቸውንና አፍራሽ ሥራቸውን እንደዚሁ በዝርዝር ይቀርባል። በውጭው ያለው የአንድነት ኃይል የኃይማኖት ተቋሙን፣ ዕድሩን፣ የኮሚኒቲ ማህበሩን መጠበቅና መከላከል ይኖርበታል።

ስለሆነም በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ የእነዚህን ሰዎች የወያኔ ተላላኪነት ባሕርይ በሚገባ አውቆ ራሱን እንዲጠብቅና ለሕዝቡና ለአገሩ መቆሙን መታገሉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ያስፈልጋል።